ሂሳዊ ድርሰት

# የሚሌኒየም እንቁጣጣሽና ተስፋ የምናደርገው

በምትኩ አዲሱ

***መቅድም***

*የሚሌኒየም ዝግጅት በአንድ መልኩ መልካምና የሚደገፍ ቢሆንም በሌላ መልኩ የተዛነፈ ጉን ይታይበታል።*

*መጀመሪያ ስም አጠራሩን እንመልከት። ቃሉ በአማርኛ ተመጣጣኝ ፍቺ ሳይገኝለት በጥድፊያ መሃላችን ገብቶ በቋንቋና በባህል ለያይቶናል። የልማትና የአስተዳደር ታሪካችንም እንደዚሁ ከዚህ ከግርግር ባህል ለመላቀቅ አለመቻሉ ሊያሳስበን ይገባል። አንዴ ዘመቻ፣ አንዴ አዋጅ፣ አንዴ ግምገማ፤ ይኸ ፖሊሲ፣ ያ ፖሊሲ እያልን ኖረናል። ባጭሩ፣ ያልተዘጋጀ አእምሮ ለኋላ ቀርነት የማያቋርጥ አሣር ነው ቢባል የተጋነነ አይሆንም።*

*2ኛው ሺህ እንዳይባል ደግሞ በአገራችን የተለመደው አባባል 8ኛው ሺህ ነው። 8ኛ ሺህ የዓለም ፍጻሜ መቃረቡንና ምልክቶቹን ጭምር አስረጅ ስለሆነ የፈንጠዝያ ወራት ሳይሆን ንስሓና ቀኖና የሚገባበት ነው። ውስልትናና ሸፍጥ ከመብዛቱ የተነሳ የእግዚአብሔር ፍርድ የሚጠበቅበት ሰዓት ነው። ሦስተኛ፣ በደፈናው ሺህኛው ዓመት እንዳይባል መከራችን እንደ ሺህ ዓመት ረዘመ ለማለት ካልሆነ በስተቀር ምንም ትርጉም አይኖረውም። ይኸ የተውሶ ሚሌኒየም እንግዲህ ማደናገርያ መሆኑ ነው። ክብረ በዓሉ የኛ፣ የአከባበሩ ባሕል ባዕድ። ፊደሉ አማርኛ፣ ገጽታው ግን ፈረንጅኛ።*

*ኦሮሚፋ ደግሞ ፊደሉ ባዕድ፣ ልሣኑ ግን ያው የኛ ነው። የሚያስተሳስረንና የሚነጣጥለን ባዕድ ይሁንን?*

***ያለፈውን እንርሳ***

*የፈረንጆች ሚሌኒየም ያስገነዘበን ነገር ቢኖር በአንድና ሁለት ምዕተ ዓመታት ውስጥ የደረሱበትን የሥልጣኔ ደረጃ አድንቀው ለመኩራራት መብቃታቸውን ነው። እርግጥ የምዕራባውያን ኑሮ ከኮምፒዩተር ዕደ-ጥበብ ጋር በመተሳሰሩ ዘመኑ ሲሸጋገር ይከሰታሉ ያሏቸው ማኅበራዊ ቀውሶች እንደ ነበሩ እናስታውሳለን። የኛ ግን ሲታይ፣ ባለፈው ታሪካችን ላይ እንኳ ገና ስምምነት የለንም፤ የጋራ የሆነ የደመቀ ታሪክ ሳይጠፋ ሁሉም በየግሉ የራሱን ማዳነቅ (የሌላውን ማናናቅ) ሁኔታ ይታይበታል። ካለፉት ዓመታት አተረፍን የምንለው የሚላስ የሚለበስ እምብዛም የለንም። አሁንም ገና በስጋትና በሰቀቀን ላይ እንገኛለን።*

*ያለፈው ይረሳና ከንግዲህ ወዲያ አዲስ አሠራር ይኑር ማለት መልካም ነው። ሆኖም እንዲህ ዓይነቱ አሳብ መቸ ተለይቶን ያውቅና ነው ማሳሰብ ያስፈለገው? ችግሩ ቀድሞውንም አሳብ ሳይሆን ተግባር አልነበረም ወይ? ገና የተስፋ ቀለብ ይሠፈርልናል። በደርግ ዘመን በተለይም በአስረኛው ዓመት ክብረ በዓል ላይ "ልማት፣ እኩልነትና ነፃነት" ተብለን ነበር። አልለማንም፣ እኩል ደኸየን እንጂ። ነፃነትማ ከቶውንም አልታሰበም።*

ዛሬ ደግሞ ይባስ ብሎ “ብሔራዊ ገጽታችንን በማደስ በጋራ አገራዊ አመለካከትና ራእይ ለዘላቂ ልማትና ለመልካም አስተዳደር ግንባታ በቆራጥነት መነሳሳታችንን ማስመስከር” ነው ተብለናል። [1] እነዚህን ቃላት ያዥጐደጐደ ግለሰብ እየሳቀ ቢሆን የጻፋቸው አይደንቅም።

“ኢትዮጵያን በሃያ ዓመት ማሌዥያ ለማሳከል ቆርጠናል” ወይም “ደርግ ያበላሸውን መሠረተ ትምህርት ለማቃናት ስንታገል ያቀድንላችሁን ተግባራዊ ማድረግ አልቻልንም” ስንባል “እንጃ፣ አሁንስ አስመረራችሁን” ብንልና ብንጠረጥር አይፈረድብንም። ኧረ ለመሆኑ፣ እስካሁን ዘላቂ ልማትና መልካም አስተዳደር የጠፋው ለምንድነው? ሺህኛው ዓመት እስኪደርስ መጠበቅ ከቶ ለምን አስፈለገ? ልንል ይገባል።

በየድረ-ገጹ የሚታተመው በቃሉ አቀራረጽና በዓላማ አፈጻጸም ዙሪያ ስምምነት አለመኖሩን ያሳያል። አንዳንዱ ምናልባት በሰበቡ አንዳች መልካም ቢመጣ ብሎ ተስፋ አድርጓል። ሌላው ለአንድ አፍታም ቢሆን መከራችንን እንርሳበት፣ ይህስ ለምን ይለፈን የሚል ነው። የተቀረው የነበረው ሁኔታ ሳይለወጥ በሌላ መልኩ እንዲቀጥል የሚፈልግ ነው።

ባጠቃላይ ግን ራሳችን ሳንለወጥ ሌላው እንዳሰብነው ሆኖ እንዲገኝልን እንሻለን። ለውጥ እንመኛለን። ፈቃደኛነት፣ በጎ ኅሊናና ፈሪሃ እግዚአብሔር ሳይኖር ዘላቂ ለውጥ እንደማይኖር ግን እንዘነጋለን። እግዚአብሔርን መፍራት ከዓለም ባንክ ድርሳን ይልቅ ለሙስና መፍትሔ ይሆነን ነበር፤ በቃልና በሥራ መታመንን ያጎናጽፈን ነበር። ምን ይደረግ? በጎ ፈቃድ ጠፍቷል። እስካሁን አብረን ካሳለፍነው ታሪካችን ውስጥ የምንማረው የማንማር መሆናችንን ነው። ለመማር በጎ ፈቃድና ትሕትና ያስፈልጋሉና። እኛም የተከበርን በተለይም የተማርን አበሾች በጎ ፈቃድና ትሕትና ይጐድለናል።

## ሚሌኒየምና እንቁጣጣሽ?

አንድ ሰሞን ወሬው “ግሎባላይዜሽን” ነበር። ወረቱ አለቀ መሰል አሁን ደግሞ ሚሌኒየም ሚሌኒየም እያሰኘን ነው። አውሮጳ ከሰባት ዓመት በፊት በልቶ የዋጠውን፣ ምድራችን ላይ የምናስገሳው ገና ዛሬ ነው።

የዘንድሮ ግርግር ይልቅ ያደግንባትን “እንቁጣጣሽ” እንዳያስረሳን!

እንቁጣጣሽ፣ እንቁጣጣሽ
እንኳን ደህና መጣሽ

እንቁጣጣሽ፣ እንቁጣጣሽ
ዓመት ዓመት ያምጣሽ



ሚሌኒየም፣ ሚሌኒየም
ምኔም የለም

ሚሌኒየም፣ ሚሌኒየም
ሚሊም የለም

## የተማሩ የምንላቸው

የተማሩ የምንላቸው ውጭ አገር የኖሩ አበሾች ወገኖቻችን እግዚሐር ይስጣቸው ሌላ ባአድ ቃል ጭነው ተጋግዘው አዲስ አበባ አድርሰውልናል። መንግሥት ተቀብሎ እናንተም ባትሉ እኰ እኔም

አስቤበት ነበር ብሎ ኰሚሽን አቋቁሞልናል፤ እንዲያውም ድ-ል ያለ ድግስ አዘጋጅቶ እየጠበቀን ነው።

ይኸውላችሁ፦ "የዓለም መንግሥታት ሆይ፣ ዋዘኞች አይደለንም፤ እኛ አበሾች ያማረብን ነን። ታሪክ ያለን ሕዝቦች ነን፤ ጥበብና ሥልጣኔም አያጣንም። አንዳንድ ጥበበኛና ምሑር ቢያስጠላንም። ሥልጣኔአችን ደግሞ አክሱም ብቻ አይደለም፤ ሐረርም የኛው ነው። ጂማ አባ ጂፋርም ገናና ነው። የቤርታና ጉሙዝ ሥልጣኔ ለአክሱምም ክብሩ ነው። የ 1000 ዓመት ታሪካችን ዜሮ ተረስቶ ኖሮ 100 ስንል ከረምን። የሦስት ሺህኛውን አከባበር ደግሞ ከኤርትራ መልስና የተቀሩት እስረኞች ሲፈቱ እናስታውቃችኋለን!

"መዛት እናውቅበታለን፤ ጠፍሮ ማሰር ቀለባችን ነው። ሰላም እናውቃለን፤ ሥራ ስንፈታ እንቆራቆሳለን እንጂ። ደግሞ ያለ ፍትህ ሰላምን ማምጣት ተችሎናል!

"ባዕዳን የሆናችሁ እናንተ አንደበታችሁን በኛ ልሳን አንዴ አሟሹት። የናንተን አሰለምዳችሁን የለ? እስቲ፣ "ሽማግሌ" በሉ፤ … ሼመገሌ … ሼ-ማ-ጊ-ሌ… ሺም-ጊሌ… ሼሜግ-ሌ

**ውስኪ በውስኪ**

የዘንድሮ መንግሥት ውስኪ በውስኪ ሊራጭብን ነው። ጭፈራ እንድታዳምቅ ለአንዲት ጥቁር አቀንቃኝ ዘመዳችን በሼክ አላሙዲ አጋፋሪነት አንድ ሚሊዮን ዶላር ቀብድ ተከፍሎ ከአሜሪካ ድረስ ተጋብዛልናለች። [2] ፈረንጅ መሆናችን ካልቀረ፣ ይልቅ በዓሉ ከመድረሱ በፊት ቶሎ ብለን የፈረንጆችን ቃላት እንሸምድድ።

"ሚሌ--ኒየም" እንበል ሁለት ጊዜ። ሚሌንየም… ምዬልየም… ምኔልየም… ምዬልነም… ልሜንየም…ልኔምየም።

"መድኃኒዓለም!" ማለት ሳይቀል አይቀርም!

ጥቁር ወገኖቻችንን "ከነጩች አናንስም" ማሰኘት ብቻውን ያሞኛቸዋልና ተንጋግተው ሊመጡልን እየተጠበቁ ናቸው። የኛን ብልጠት እንደሆነ ምንጊዜም መረዳት አይችሉ፤ ለኛም እንኳ ተሰኖናል። እና እስኪነቁብን ሺህ ዘመን ያልፋል።

ለማንኛውም ሦስት መቶ ሺህ እንግዳ ከውጭ አገር ይጓጓዛል ተብሎ እየተጠበቀ ነው። ሚሌኒየሙ ሊደርስ አርባ ቀን ቀርቶታል። የመንግሥት ዜና ምንጭ እንደ ዘገበው ከሆነ፦ "ባለፈው አንድ ወር ውስጥ ከስምንት እስከ 10 ሺ የሚደርሱ እንግዶች ወደ አገር ውስጥ መግባት መጀመራቸውን" ገልጿል። [1] ገብተዋል ወይስ አልገቡም? ለምን አስረግጠ "ገብተዋል" እንዳላለ አልገባንም።

እንግዲህ ሺህ መንገደኛ በአንዴ የሚጐርስ አውሮፕላን ዛሬ ቢፈጠር እንኳ በሚቀሩን አርባ ቀናት በየቀኑ 13 አውሮፕላን ከነ ሰንቁ፣ ከነአብራሪዎቹና አጋፋሪዎቹ ጋር ያስፈልገናል ማለት ነው። የእስራኤል መንግሥት ፈላሻ ወገኖቻችንን አጣድፎ እንዳጓጓዘ ሁሉ ይጠየቅልን ይሆን? ለማንኛውም አየር መንገዳችን ተጨማሪ ማጓጓዣ ተከራይቶልናል። መዲናችንም እነሆ፣ ሚሌኒየም በሚሌኒየም ሆና ተዘጋጅታለች።

- "ሚሌኒየም ሬስቶራንት" (እዚህ የተመገበ በሺህ ዓመት ሆዱ አይጐድልም፤ ችግሩ ግን ወረፋው አያስቀምስም)
- "ሚሌኒየም ጠጅ ቤት" (እዚህ የተጐነጩ ለሺህ ዓመት …፤ ሲነቃ ምን ዓይነት መንግሥት ይጠብቀው ይሆን?)
- "ሚሌኒየም አደባባይ" (እዚህ የተረማመደ ሲጓዝ ቢውል አይደክመው)
- "ሚሌኒየም ስንዴ" (ከተዘራ ጉልጓሎ አያሻውም፣ ማጨድ ብቻ ነው)
- "ሚሌኒየም ልማት" (ድህነት ደህና ሰንብች)
- "ሚሌኒየም ኰሌጅ" (ጥናትና ፈተና የለበት፣ ማሰብ አይጠይቅ፣ ዲፕሎማ ብቻ)
- "ሚሌኒየም ቤተ ክርስቲያን" (የኛ አባል የሆነ እንደ ማቱሳላ ዕድሜው ይረዝማል)
- "ሚሌኒየም ሴክሬቴሪያት ጽ/ቤት" (ሴክሬቴሪያትና ጽ/ቤትን ምን ለያቸው?) [1]

ግርግር ብዙ ያሳያልና በዕለቱ የሚወለዱ ሕጻናት "ሚሌነም" ቢባሉ አይድነቀን! ነፍስ ያላወቁ ሕጻናት "አብዮት" ተብለው የለ!

እነዚሁ ነፍስ አውቀው ተማሪ ቤት መሄድ ሲጀምሩ፦ ስማቸው "ሚሌነም ይሄይስ" "ሚሌነም ገብረ ክርስቶስ" "ሚሌነም ረጋሣ" ይሆናል ማለት ነው። ወይም "ሚሌነም ሽብሩ" "ሚሌነም ነፃነት" "ሚሌነም ካሣ" (የመምሬ ካሣ ልጅ) "ሚሌነም ጐይቶም" (የአቦይ ጐይቶም የክርስትና ልጅ) "ሚሌነም ኸጀሌ" "ሚሌነም በፈቃዱ" "ሚሌ 'ሚሊቱ' ሚሌነም" (የሚሊ ጓደኛ) …

ማን ያውቃል፣ እድሜ ለዚህ መንግሥት አንለምንም እንጂ በሦስተኛው ሚሌኒየም "ሚሌኒየም አከሌ" የተሰኘች ጠቅላይ ሚኒስትር ትገዛን ይሆናል። ከዚያ በፊት ክርስቶስ ካልመጣ።

**አዲሳባ እንሂድ**

ከውጭ አገር የሚሄድ ሰው ባይኖር ይኽ ሁሉ ዝግጅት ይደረግ ነበርን? የመንግሥት ደስታ የሕዝብም ደስታ የሆነበት ዘመን ትዝ የሚላቸው ሰንቶች ይኖራሉ? የሕዝብ ደስታ ለመንግሥት ራስ ምታት የሆነበትስ? ከዚህ የተነሳ ይመስላል፣ አንዳንዶች ወገኖቻችን አዲስ አበባ መሄድ አያሻም እያሉ ነው። ኢትዮጵያዊነት ኢትዮጵያ አፈር ላይ በመቆም ብቻ አይወሰንም፤ የዚህ መንግሥት ሥራ ስላላማረን እዚሁ ባእድ ምድር ቆመን እየተቃወምነው ዘመኑን እንቀበላለን እያሉ ነው። አገር እኛ እንጂ አፈሩ አይደለም የምትለዋን አባባል እንኳ አሉላ አባ ነጋ እንዳይሰሙ። ምናልባት ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ ስለሆነች የምድር ሕዝብ ሁሉ የኢትዮጵያዊነት ቁራጭ አያጣም ማለት ያዋጣ ይሆናል።

ለማንኛውም፣ የአሜሪካን መንግሥት መቀመጫ የሆነችው የዋሽንግተን ዲሲ ከንቲባ "የኢትዮጵያ ሚሌኒየም" ጽዋ የትም አይሄድም እዚሁ እንቃመሳታለን ብሏል አሉ። ሆድ ለባሳቸው ጥሩ ማስተዛዘኛ ተገኝቷል። "ከነጮች አናንስም፣ ገና 2ሺህም ቢሆን እኛም የተከበርን ጥቁሮች የራሳችን የምንለው ዘመን አቆጣጠር አለን" የሚሉ 50 ሺህ የሚደርሱ የተከበሩ አበሾችና ጥቁር ፈረንጅ ዘመዶቻችን ይተባበሩናል ተብሎ ይጠበቃል። [3] እንዲያውም ክብረ በዓሉ ላይ የሚገኝ ሁሉ ከዕድሜው ላይ ሰባት ዓመት ከስምንት ወር ከአሁኑ መቀነስ እንዲጀምር ተወስኗል።

**ጭንቅላትክን ግዘፍበት**

እንግዲህ ዓለም ካዳነቀልን ከዚህ ወዲያ ምን እንፈልጋለን? መንግሥት እንዳይሳከርና ቋጥሮ የኖረውን ምሥጢር እንዳይዘረግፍ ብቻ! ጦር ሜዳ እንዳይማግደን ብቻ! ወይንም ከሥልጣን አርካብ ላይ ሳይታሰብ ተንሸራትቶ እንዳይወድቅብን!

የተወራለት ይኸ ሚሌኒየም ሊደርስ አሁን አርባ ቀን ከአርባ ሰዓት ከአርባ ደቂቃ ከአርባ ሴኰንድ ቀርቶታል... ምነው ቶሎ በደረሰ... መጠበቁ ጨረሰን አይደል? ቶሎ በጨፈርንና ባረፍነው... ተሳክረን ያለፈውን ዘመን በረሳንበት...

ጭፈራ ግን የደስታ ምልክት ላይሆን ይችላል፤ እንዲያውም ንዴትና ፍርሃት ሲበዛ ወደ ሣቅ ይቀየራል ይባላል! "በሳቅ ደግሞ ልብ ያዝናል" [9 ሀ]

ደንስ ጐበዝ! ደንስ ጀግና
ክራቫትክን አውልቅና
ሃሳብክን ልቀቀውና
ኮትክን ሸሚዝክን ጣልና
ርገጥ፣ ጨፍር፣ ደንስ ጀግና
...

ጭንቀላትክን ግዘፍበት፣ ውቀጥበት፥ ውገርበት፣ ...
ዝግ ብሎማ ያሰበ እንደሁ፣ ይነግርሃል አንዳች እውነት! [4]
[ጸ.ገ.መ፤ እሳት ወይ አበባ፤1963]

## የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊያልፍለት

ኢንተርኔት፣ ሞባይልና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ይህን ታሪከኛ ቃል አሳፍረው ሊያንበሸብሹን ሽር-ጉድ እያሉልን ነው። አዲሳባ ከደረሰ ደግሞ እንደ ምንም ሎንቺና ተሳፍሮ ደብረ ዘይትና ናዝሬት መውረዱ አይቀርም።

የጤና ያርግልን...

እንግዲህ ከተሜው ሚሌኒየም ሚሌኒየም ካለ በቂ ነው፤ ከዳር ዳር ተዳርሷል ማለት ነው። ሌላው ሕዝብ ድሮም ከቁጥር አይገባም።

"የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ስንት ነው?" ቢሉት

"ይህን ያህል ነው ይባላል" አለ

"እነማንን ቆጥረህ ነው? እኛ ባለሥልጣኖቹና ዘመዶቻችን ብንደመር አምስት መቶም አንሞላም"

## እኛና ፈረንጆች

የፈረንጆቹ ሚሌኒየም የዛሬ ሰባት ዓመት አስጨንቆ አስፈንጥዞ አልፏል። እንደ ተፈራው ምድረ ዓለሙ አልተገለባበጠም። የሆነውና የተወራው ግን ትዝብት ጥሎ አልፏል። ለካንስ ሁዳድ ሙሉ ጀግና የሚመስለው መልኩን አሳምሮ ጸርጻራ ኖሯል!

ምጽዓት ይኸውላችሁ ያሉን አንዱም አልያዘላቸውም። የግርግር ነቢያት ስንቱን አሞኝተው ዘርፈዋል። ድሮስ የክርስቶስን ዳግም ምጽዓት ማን ያውቅ ኖሯል?

ፈረንጆች ይህን የአከባበር ፈሊጥ ባያመጡ እኛስ የተከበርን አበሾች በራሳችን እናስበው ነበር? እንጃ፣ አይመስለኝም። ቀልቦ የራስ ማድረግ ነው የሚቀናን፤

ለመሆኑ ሚሌኒየም ምንድነው? እንደ ቋንቋ ሊቃውንት ከሆነ ሚሌኒየም ቃሉ ሺህ ዓመት ማለት ነው። የትኛውን ሺህ ዓመት ማለቱ ይሆን? ስንት ሺህ ዓመት አለና ነው? የሚታወቀው ሺህ ዓመት አንድ ብቻ ነው። ተስፋና ፍትህ የሚፈጸምበት፣ ጽድቅና ቅድስና የሚታይበት፣ ደስታና እርጋታ የሚሰፍንበትና ክርስቶስ ዳግም ተመልሶ ምድርን የሚገዛበት ዘመን። መጽሐፈ ራእይ (20፡ 1-6)።

በሌላ አነጋገር ሺህኛን ዓመት ከክርስቶስ ነጥሎ ማሰብ አድካሚና የማይቻል ይሆናል ማለት ነው። በግርግር መሃል ቀዳሚ ሊሆን የሚገባው ተዘንግቶ እንዳይሆን!

እርግጥ እንግሊዛዊው ኤድዋርድ ጊበን (ጥሬ ገብስ ይቃምና) "አበሾች ዓለምን ዘንግተው ዓለምም ዘንግቷቸው ሺህ ዓመት አንቀላፉ" ብሎናል። [5] አያ ጊበን ምንድነው የሚለን? ጆሮው ባይሰማለት ድምፅ አላሰማችሁም ነው? ዐይኑ ባያይለት አልታያችሁም ነው?

ዓለም እንግሊዝ ነው ማን አለ? ከኢየሩሳሌም ጋር ቃል ከተጋባን ዓለምስ እኛ ነን። ምን ይደረግ፣ ምጽአት ለእንግሊዝ ስንቱ ነው። እኛ ግን የተኛን ስንመስል ብራና ላይ የወንጌል ቃል እና-ትም እንደነበር ለጊበንና ለዘመዶቹ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ይንገሩልን!

**ካንጀት ካለቀሱ**

ሺሁስ ዓመት ከመቸ ጀምሮ ይሰላ? ጥያቄው ይኸ ነው። ከ 982 ዓመተ ምሕረት ጀምሮ ቢሰላ ሚሌኒየሙ የዛሬ አሥር ሰባት ዓመት ይሆን ነበር ማለት ነው፤ የጉስቁልናችን ሕመሙ እንዲህ ባልበረታና ባልተራዘመ?!

ይኸስ ሚሌኒየም ላገራችን ያስፈልጋት ነበር? ደግሞስ ለምን አሁን?

አንዳንዶች እንደሚያስረዱን ከሆነ፦ ሺህ ዓመት አንዴ የሚመጣ ስለሆነ እንዳያመልጠን ነው፤ ይህን ዕድል መልሰን አናገኘውም ነው! ለነገሩ አንድም ቀን ቢሆን አንዴ ብቻ ነው የሚመጣው። የሚደገም የለም። ሁሉም ኃላፊ ወይም መጪ ነው። በኃላፊውና በመጪው መካከል ተንጠላጥለን መኖዝ ዕጣችን ነው። የዛሬውን ካላወቅንበት ሳያውቀን ያልፈናል። ሺህ መሆኑ ድንቅ አይደለም ማለት ነው። ደግሞ ተሐድሶ ለአገራችን ስለሚያስፈልጋት ነው ይሉናል። እርቅ ይውረድ፣ በዓለም ሕዝቦች ዘንድ ጉስቁልናችን በዛ እኮ፤ ባለ ታሪክም እንደሆንን ይዩ እንጂ...

አያምጣና፣ የዛሬ ዓመት በአንድ ጉዳይ ላይ መግባባት ቢጠፋ ሌላ ሺህ ዓመት ሊጠበቅ ነው? ቀልዱን እንተወው! ከደርግ ዘመን ጀምሮ ተሐድሶና ልማት እንደተባልን ነው የኖርነው። መንግሥት እስከ መቸ ነው እንደ ልጅ የሚያየን!?

**ከልብ ካዘኑ**

እርቅና ሰላምማ የዛሬም ሁለት ዓመት ይሆን አልነበረም? ሚሌኒየም ሳይባልም እንቁጣጣሽ ‘ለት ሊሆን ይችል አልነበረም? እርቅና ሰላም በፍንዳታና በአዋጅ ሳይሆን በየዕለቱ በግለሰቦች፣ በቤተሰብና በጐረቤት መካከል፣ በሃይማኖትና በፖለቲካ መሪዎች መካከል፣ በሕዝብና በመሪዎች መካከል ተግቶ የሚደረግ ጉዳይ ነው። ለመሆኑ የሃይማኖትና የመንግሥት መሪዎቻችን ሕዝቡን ሰላደረሱበት ጉስቁልና ይቅርታ የሚጠይቁበት ጊዜ መቸ ነው? እርቅና ሰላም የዕለት ተግባር ነው። ምግብን ባንዴ ካጋበሱት ትርፉ ቁንጣን ነው። ለጤና እንዲሆን ከተፈለገ በመጠኑ በሰዓቱ መመገብ ይገባል ማለት ነው። “አገራዊ ራእይና አመለካከት” ባለፉት 17 ዓመታት ቅዠት ከመሰለ ሚሌኒየሙ ደርሶ ምን ያህል ያጠራዋል?

መሸነጋገል ቢቀር ምን አለበት? የአገር መሪዎችስ አርኣያነት እስከ ምን ድረስ ነው? የሚያሰሙን ንግግር የሚያረጋጋ ነው ወይስ የሚያሸብር? ተስፋ የሚሰጥ ወይስ ተስፋ የሚያስቆርጥ? የሚያስተማምን ወይስ አለመተማመንን የሚዘራ?

የምድራችን አየር ሲታደስ የልምላሜ ጸጋ ሲላበስ የመስቀል ወፎች ብቅ ሊሉ አለባበሳቸውን ሲያስተካክሉ የበቆሎ እሸት ሲጋጋም የወለጋ አንጨቴ ሲቆረጥ ከልብ ካሉ እርቅ ያኔስ ይሆን አልነበረም? ለአዲሱ ዘመን መንፈስ ሲዘጋጅ ያኔ ፍካሬ ኢየሱስ ይመስል፦ “ሚሌኒየም ሊደርስ ነው፣ ሚሌኒየም ደረሰ” ከማለት፣ “ጳጉሜን ልትገባደድ አንድ ቀን ቀራት” ማለት ይቀል አልነበረም?

እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ሚሌኒየም ያስፈለገው ቃሉ የተመረጠው ዳንኪራውም የተቋጠረው ለአገሬው ሕዝብ ሳይሆን ለባዕዱ ነው። ለመታያ ነው። ለንግድ ነው። የሚያተርፉ አሉ። ትርፍ በደል አይደለም፤ ፌስታም በልኩ ቢደረግ በደል አይሆንም። ስሕተቱ እቅጩን ከመናገር ይልቅ ማሳበቡና ማመካኘቱ ላይ ነው።

ደግሞ ሚሌኒየም ያስፈለገው ለፖለቲካ ነው። አሜሪካኖችንና አውሮጳውያንን ላለማስቀየም፣ በዓይናቸው ፊት እርቅና ሰላም ፈላጊና ፈጣሪ ለመምሰል፣ ድርጎ ለመቀበል ነው። የሕዝቡን ልብ ለመስረቅ። ተቃዋሚዎችን ለማሳጣት። ራስን ለማድነቅ። “አስራ ሰባት ዓመት ገዝተናል፤ ሌላ አስራ ሰባት ይቀረናል” ለማለት ነው።[6] ስለ ጀግንነታችን እንጠጣበት! እንብላበት! ለማለት ነው።

አሁንም፣ ለሕዝቡ አሳቢነታችንን ለማሳየት በቅድሚያ የጤፉንና የበርበሬውን የዶሮውን ዋጋ እናንረው። ሚሌኒየም መዳረሻ ላይ እንልቀቅለት። ሆዱ ከሞላ ጦር ሜዳም ቢሆን ይከተለናል። ጠባዩን ካሳመረ ደግሞ እድሜ እንቀጥልለታለን። ግን የምርጫ ድምጻችን ጉዳይ ምን ላይ ደረሰ ማለት ካበዛ ገና ትምህርቱ አልገባውም ማለት ነው፤ እናጠብቅበታለን። ተቃዋሚውስ ቢሆን እኛ ለሕዝቡ ካሰብንለት ምን የተለየ ትንግርት ያመጣ ኖሯል?

ቤተ ክርስቲያንም ከመንግሥታችን ጋር ሚሌኒየሙን እንቀበለው እያለችን ነው። ስለ ምጽዓትና ስለ ፍትህ የምታስተምረዋ አቋሟን መለየት ተስኗታል። ሚሌኒየሙ ከዳግም ምጽዓት በልጠባት እንዳይሆን ብቻ! መረሣት የሌለበት ጉዳይ ቢኖር ሰላምና ፍትህ በአዋጅ ብቻ እንደማይጸና ነው። የሰው ልብ በተለይም የመሪዎች ልብ ንስሃ እስካልገባው ድረስ፣ የእግዚአብሔር ፍርሃት እስካልገዛው ድረስ መሸነጋገል ይሆናል።

**የሚሌኒየም ማግስት**

የሚሌኒየሙ ማግስት ምን ያመጣልን ይሆን? ነገር እንደ ነበረ ከቀጠለ ጉድ ሆንን ማለት ነው። ለሁሉም የሚብቃቃ ሰላምና ፍትህ ከሌለ ይህ ሁሉ መደናቆር የባሰ አለመተማመን ማጥ ውስጥ ሊከተን ነው። የአንድ ጎሳ፣ የአንድ ሠፈር ልጆች የአገሪቱን መሪነት መያዛቸው ቀርቶ አመራሩ ይሰባጠር እንጂ። ቤተሰባዊ ዘውድ አገዛዝ በተሻረ በሠላሳ ሦስት ዓመቱ ”አብዮታዊ ዴሞክራሲ”ን ተላብሶ ብቅ ማለቱ አሳፋሪ ነው። አንድ መንግሥት የአገሬው ሕዝብ ሙሉ ድጋፍ ተነስቶት በባዕዳን ድጋፍ መቆሙ አሳፋሪ ነው። አገሪቱ ያፈራቻቸው ባለ ሙያዎች ቦታ ቦታቸውን ይያዙ እንጂ። ኢትዮጵያ ከአንድ በላይ ባለ አእምሮ አላፈራችምና ነው? ውሎ አድሮ የምንጐዳው እኛው የተከበርን አበሾች ነን። እነ ዶክተር ያዕቆብ ኃይለማርያምን የመሳሰሉ ባለሙያዎችን በሥራ ወጥሮ ማሠር ሲገባ ሥራ አስፈትቶ ማኖር አሳፋሪ ድርጊት ነው።

ደግሞ ከእንግሊዞችም እንማር። የመንግሥታችን አማላጅና የበላይ ጠባቂ የነበሩ ክቡር ቶኒ ሰኔ ወር ላይ የታላቋ ብሪታኒያ ጠቅላይ ሚኒስቴር እንደ ነበሩ የሚታወስ ነው። ከሐምሌ ወር ወዲህ ግን አረብ ምድር እንደ ማንም ሰው ሽቀላውን ተያይዘውታል።

ክቡር ቶኒ ሥልጣን ቢለቁም ሥልጣኑ አሁንም የፓርቲአቸው ነው እንዳንል፤ አደራ እንጠንቀቅ። ቀድሞውንም የፓርቲው አባላት የሚመለመሉት በጕሣ፣ በዝምድናና በጋብቻ ሳይሆን በችሎታ፣ በብሔራዊ ዓላማና ለአገር ዕድገትና አንድነት በሚሰጡት ጥቅም መሆኑን ማጤን ይበቃል!

እንግዲህ፣ ሚሌኒየሙ ከግርግሩ ሌላ ምን ለውጥ ያመጣልን ይሆን?

ቅያሪ መንግሥት ያመጣልን ይሆን? እስካሁን ያየናቸው የአገዛዝ ስርአቶች፦ “አደንቁረህ ግዛ” “ረግጠህ ግዛ” “ከፋፍለህ ግዛ” ና “አደናግረህ ግዛ” ናቸው። “አስተባብረህ ግዛ” ከአዲሱ ዘመን ጋር ይወለድልን ይሆን? ሕዝብና መንግሥት ሁለቱም እያማጡ ናቸው...

እንደሚወራው ከሆነ የቀደሙት የህወኃት መሪዎች ላዲሱ ሚሌኒየም የሚደርስ አዲስ ዴሞክራዊያዊ ፓርቲ ሊያቋቁሙልን እየተጣደፉ ነው፤ አሰብንም ሳያስመልሱልን አይቀሩም ይባላል። [7] ክቡር ሰዬም ለአባልነት ተጠይቀው እያሰቡበት እንደሆነ ሰምተናል። አዲስ ቅንጅት ይቋቋም ይሆን? ኢህአዴግ “ግንባር” መሆኑ ቀርቶ የ“ቅንጅት”ን ፊት፣ እጅና እግር ተላብሶ ብቅ እንዳይል! እስካሁን ያላየነውን ምን ለውጥ እናይ ይሆን? አለባብሰን ስናርስ እንዳንገኝ ብቻ!

## ያጫጭሮች አስተዳደር

ፕሮፌሰር ተኮላ ሐጎስ ያለፉትን ሦስት መሪዎቻችንን ቁመናና ምግባር አጢነው በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ቁመት ላይ ገለጻ ሰጥተውናል። [8] እንደሚሉት ከሆነ የቁመታቸው ማጠር ጠ/ሚኒስትሩ ለራሳቸው ያላቸውን ግምት አዛንፎታል፤ አስተዳደራቸውን የፍትህና የቁም ነገር ቃና ነስቶታል። ስለዚህም ከንግዲህ እንደ ማሞ ውድነህ ዘለግ ያለ የተመለመለ ቁመና ያለው ሰው ይፈለግ ብለውናል። ክቡር አቶ ሰዩም መስፍንስ ይሆናሉ? ከጋምቤላና ከሰላሌ ወገኖቻችንስ እንዴት አንድ ሰው ይታጣል?

መቸም አስተዳደር በቁመት ነው ብሎ መደምደም ባይቻልም የአፄ ምኒልክ ቁመታቸውና ብልህ አመራር ይታወሰናል። ምኒልክ እንከን-የለሽ መሪ ነበሩ ባንልም አንኮበር መወለዳቸው እንደ ኃጢአት ተቆጥሮ ለብዙ ነቀፌታ ዳርጓቸዋል። የሚያሳዝነው ግን አዱ ጉደም ወይም ቦጂ ጨቆርሳ ተወልደው ቢሆን ኖሮ ይኸ ሁሉ አሣር ባልደረሰባቸው፣ እንዲያውም ወደር የማይገኝላቸው ጀግና

በተባሉ ነበር እንላለን! ለማንኛውም፣ የሚሌኒየም ማግስት እግዚሐር ይሁነን ማለት ጥሩ ጸሎት ነው…

## ማጠቃለያ

መሸነጋገሉን እንተውና ከልብ ሰላም ያውርድ እንበል። የኛም ድርሻ ስለሚኖር ሰላም እንዲሆን እንትጋ። ሚሌኒየም የምትለዋን ቃል ደግሞ አናጥብቃት። ብዙ ጫጫታ አሰምታናለች፤ ብዙ ቀለምና ወረቀት ፈጅታብናለች። እንደ አባቶቻችንና እንደ እናቶቻችን "እንቁጣጣሽ፣ ዓመት ዓመት ያምጣሽ" እንበል። ሴቶች እልል ይበሉ። ጉበዛዝትም።

ፈሪሃ እግዚአብሔር ይኑረን። ክቡር ሰዬ ይሁኑ ኢንጂኔር ኃይሉ ምን ያህል ብርቱ ምን ያህል የተማሩ የተመራመሩ ቢሆኑ ብቻቸውን አይጠቅሙንም። በአንድ ብርቱ ላይ መደገፍ እስካሁን አልጠቀመንም። ቴዎድሮስ ቁጡነቱ አነዋወጠን፤ ኃይለ ሥላሴ ረሱን፤ መንግሥቱ በተነን፤ ይኸ መንግሥት ልዩነታችንን በማጉላቱ አነካከሰን። ዮሐንስና ምኒሊክ ብቻ አስተራረቁን። በመሪዎቻችን መካከል ያለው ልዩነት ሕዝብን ለአንድ ዓላማ ማስተባበር በመቻላቸውና ባለመቻላቸው ላይ ነው። በእግዚአብሔር ፍርሃት የሚያነሳሱና የሚያያይዙ ለሕዝብ የሚራሩ ለምቾቶቻቸው የማይሳሱ የአገርን ክብር የማያስደፍሩ ለሕዝብ ኃፍረት ያልሆኑ የሕዝብን ሥነ ምግባር የሚገነቡና የሚያከብሩ ብቃት ያላቸው ሰዎች ያስፈልጉናል። አምላክ ይርዳን!

የጳጉሜን ወር ማልደን ተነሥተን ገላችንን እንታጠብ። ስድስቱንም ቀን እንታጠብ። ያረጀው፣ አድፋና ጥሉ፣ ቁርሾና ብቅሉ ይወገድ። በሰባተኛውም ቀን መዝሙረ ዳዊት አንስተን እንድገም፦

አቤቱ፣ እንደ ቸርነትህ መጠን ማረኝ
እንደ ምሕረትህም ብዛት መተላለፌን ደምስስ
ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ
ከኃጢአቴም አንጻኝ

ከኃጢአቴ ፊትህን መልስ
በደሌንም ሁሉ ደምስስልኝ…
አቤቱ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ
የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ

የማዳንህን ደስታ ስጠኝ
በእሽታ መንፈስ ደግፈኝ [9 ለ]

**Copyright August 4, 2007 by Mitiku Adisu. All rights reserved.**

## መረጃዎች

[1] Ethiopia2000.com [The Official Millennium Page]
[2] http://www.beyoncestar.com/
[3] Ethiopianmillennium2000.com [Washington DC]
[4] እሳት ወይ አበባ፣ ጸ.ገ.መ.፣ ብሰማቤ፣ 1963

[5] John Gunther, *Inside Africa*, 1955, p. 247
[6] Stephanie McCrummen, Interview With Meles Zenawi. Washingtonpost.com
[7] Former TPLF Members to Establish New Party, www.addisfortune.com
[8] EDITORIAL: The CUD/Kinijit Opposition Leaders: Life Sentence/Pardon**,** www.tecolahagos.com
[9] መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሀ. መጽሐፈ ምሳሌ 14፥13። ለ. መዝሙረ ዳዊት፣ ም. 51። 1962 እትም